**የተቋሙ የሰዉ ሃይል**

ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር 89/2002 ዓ.ም እንደገና ተሻሽሎ ከተቋቋመ በኋላ በስራ አመራር ልማት ዋና የስራ ሂደት/በአሁኑ አጠራር የስራ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት/ ውስጥ የሚሰሩ አሰልጣኞች እና አማካሪዎች በቦርድ ሲተዳደሩ ሌሎች ደጋፊ የስራ ሂደት በሲቪል ሰርቪስ እንዲተዳደሩ ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ሰዓት 8 ዳሬክቶሬቶቸ ሲኖርው በአጠቃላይ 102 ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ሲኖሩት ከነዚህም ውስጥ 10 የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ዋና አማካሪ፤ከፈተኛ አማካሪ እና ረዳት አማካሪዎች ናቸው ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ በአሁን ሰዓት ያለው የሰልጣኞች ማደርያ አልጋዎች ወይም በአንድ ስልጠና ስልጣኞችን ተቀብሎ የማሳደር አቅሙ ከ250-300 ሲሆን በተመሳሳይ መልኩም እያንዳዳቸው 45 ሰልጣኞችን የሚይዝ 10 የስልጠና ክፈሎች ያሉት ሲሆን የመሰብሰብያ አዳራሻን በተመለከተ ስንመለከት ደግሞ የመያዝ አቅሙ 150—200 ሰልጣኞችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል የመሰብሰቢያ አዳራሽ የሚኖር ሲሆን ተቋሙ በየዓመቱ መደበኛ ስልጠና ከመስጠት አንጻር ባለፉት ሁለት ዓመታት በክልሉ ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ከመተከል እና ከካማሽ ዞን ምንም አይነት ሰልጣኝ ባለመምጣቱ ምክንያት የመደበኛ ስልጠናዎቻችን በአሶሳ ዞን እና በክልል ተቋማት ላይ ብቻ ተወስኖ በመቅረቱ በመደበኛ ስልጠና የሚሳተፉ ሰልጣኞች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ የሚገኝ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሙ ተቋሙ የሚያስተባብራቸው ስልጠናዎች የሰልጣኖች ተሳትፎ ባለፉት አመታት ከነበረው በማድግ ላይ ይገኛል፡፡

**የተቋሙ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሩ ሁኔታን በተመለከተ**

በተቋሙ በምስረታ ዘመኑ ከነበረው ሁኔታ አንጻር ከፍተኛም ሆነ መካከለኛዉ አመራሩ ሠራተኞችን አስተባብሮ የመምራትና ወደ ሥራ የማስገባት፣ የስትራቴጂውን ምንነትና ፋይዳ ላይ ሁሉም በተመሳሳይ ደረጃ ዕዉቀት ያለዉ ባይሆንም ስራዎችን የማቀድ፣ፈፃሚ የማዘጋጀት፣ የማስፈፀምና በየደረጃው የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋትና የተሰጠውን ተልዕኮ በመያዝ በየዳይሬክቶሬቱ የሚገኙ ሠራተኞች ያሉባቸውን የአመለካከት፣ የክህሎት፣የመልካም አስተዳደር እና የአቅርቦት ችግሮችን እየተከታተለ የአመላካከት ፣የክህሎትና የአደረጃጀት እንዲሁም አሰራር ክፍተቶችን በመለየትና እነዚህን ማነቆዎች ለመፍታት የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማቀድና አፈፃፀማቸውን ከመምራት አንጻር አበረታች ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ የእቅድ አፈጻጸሙን በየወቅቱ በተለያዩ መንገዶች በመከታተል ወቅታዊ እና ትክክለኛ የመፍትሔ ሀሳብ በመስጠት፣በየጊዜዉ የመገመገም አሰራር አጠናክሮ ሲያርም የቆየ ሲሆን ይህንን ዉጤታማ በሆነ መንገድ ሲያካሂድም እያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ ከነበረው በተሻለ መልኩ የክትትል እና ድጋፈስራዎችን ሲገመገም ቆይቷል፡፡ሆኖም ግን አሁንም ሥራዉን ተቋማዊ ከማድረግና ሥርነቀል ለዉጥ ከማምጣት አንፃር ገና ብዙ መሥራት ይጠበቃል፡፡

**2.2.2 የሠራተኛዉ ሁኔታን በተመለከተ**

ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ ከነበረው ተቋማዊ እሴቶች ላይ የተጠናከረ ስራ አለመሰራት ሲስተዋል የነበሩ የአመለካከትና የክህሎት እንዲሁም የአገልጋይነት ስሜት ደካማነት ችግሮች ሲሆኑ ከጥቂት አመታት ወዲህ ግን የተቋሙ ሰራተኞችን በተለያዩ የለውጥ ፕሮግራሞች ላይ ስልጠና በመስጠት ፣የውይይትና የግንዘቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ተቋማዊ እሴቶች ላይ ሰፊ ስራዎችን በመስራት በሰራተኞች ላይ የስራ መነቃቃትን ለመፈጠር ተሞክሯል፣ በሰራተኛው መሀል ጤናማ የስራ ውድድር እንዲኖር ዘረፈ-ብዙ ስራዎች እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን ጥሩ ስራዎች ቢሰሩም በስልጠና የተገኘዉን ክህሎት ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ አለማዋልና በሰራተኞች መካከል የክህሎት ሽግግር አለማድረግ፣ በተወሰነ መልኩ የአገልጋይነት እና ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ክፍተት የሚታይባቸዉ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል ፡፡